# ይድረስ ለዕጬ 'ጠቅላይ ሚንስትራችን' ኃይሌ ገ/ሥላሤ

ነጻነት ዘገዬ

የኢትዮጵያን ወቅታዊ ጉዳይ ይሁነኝ ብሎ ለሚከታተል የውስጥም ሆነ የዉጭ ታዛቢ በዬዕለቱ አዳዲስ አስገራሚ ነገር አያጣም:: «ቀን የሰጠው ቅል . . .» እንዲሉ ጊዜ የሰጠው ሞልፋጣ ሁሉ ባልተገራ ስድ አንደበቱ ሕዝብን ባገኘው አጋጣሚና መድረክ እዬተነሣ ሲሳደብ መስማት ደግሞ የዘመናችን ፋሽን ሆኖ ከመገኘቱም በላይ ይህ በአሳዛኝነቱ ከሁሉም የሚበልጥ ሀገራዊ ጉዳይ ሃይ የሚለው ማጣቱ ይበልጥ ያስገርማል::

በውነቱ እኛ ኢትዮጵያውያን በብዙ ነገር አልታደልንም:: የደርግንና የወያኔን የግፍ አገዛዝ ቀምበር አለውድ በግዳችን - ያው የፈረደበት ቀን ጥሎብን - መሸከማችን ሳያንሰን በሞራልም ሆነ አቅማችን በፈቀደው ሌላ ነገር እየደገፍን እኛው በኛው ላይ ያነገሥናቸው የገዛ ልጆቻችን ተመልሰው እኛኑ ሲሳደቡና መጎናበሻ ሊያደርጉን ሲቃጡ «እባካችሁ ወደ ልቦናችሁ ተመለሱ» የሚላቸው መካሪ መጥፋቱ በእጅጉ ያሳዝናል:: እነዚህ የበሉበትን ወጭት ሰባሪዎች ሲያጠፉ ማስተማር፣ ከመስመር ሲወጡ ለመመለስ መሞከር፣ እምቢዬው ብለው በያዙት የጥፋት መንገድ ሲጉዋዙ ገመናቸውን በግልጽ አውጥቶ ለሌሎች ማስተማሪያነት ማዋል ሲገባ ዝም ብሎ መቀመጥ «የምታደርጉት ነገር ጥሩ ነው፤ ግፉበት» እንደማለት ነው:: ይህ ዓይነቱ ይሉኝታ ደግሞ ብዙ ጎድቶናል:: ዝርዝሩ በይደር ይቀመጥ::

ሰሞኑን ዕጬ ጠ/ሚንስትራችን ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሤ ተናገረው የተባለውን ስሰማ ኮረንቲ ልጨብጥ ምንም አልቀረኝ፤ ከኮረንቲው የተሻለ መንገድ ስፈልግ ይቺን ጦማር መጦመር ትዝ አለኝና ብዕር ቢጤ አነሣሁ:: ብዕሬን ከወረቀቱ እንዳዋደድኩ እንዲህ ብዬ መጀመር ፈለግሁ፤ እንዲህ - «ይሄ ድህነታችን ገና የማያሰማን የለም ማለት ነው? ብርቅዬ ልጆቻችንን ከጉያችን እዬቀማ የሚወስድብንስ እስከመቼ ነው? ሮጦም ፣ሰርቆም፣ አጭበርብሮም፣ ዘርፎም፣ ሞስኖም ፣አገር ሽጦም፣ ዓላማውን ሽቅጦም ፣ አስተብትቦና አስጠንቁሎም . . . የደለበ ሀብት ያገኘ ሁሉ ከሜዳ እዬተነሣ ምሥኪንና ድሃ ሕዝብ ላይ የሚያቀረሽ ከሆነ ለወደፊቱ ምን ሊውጠን ነው? የሀብትና የሥልጣን ማደላደያው ሕዝብን መናቅና ማዋረድ ይሆን? በሕዝብ ላይ መታበይ፣የወጡበትን መሰላል ሰባብሮ መጣል ፣ ለተረገመ ዓላማ ከርጉማን ጋር ተሠልፎ አገርንና ወገንን መበደል የወቅቱ ኢትዮጵያዊ ሥልጣኔ ሆነ ማለት ነው?» ብዬ ጻፍኩና ደግሜ እያነበብኩ በእጅጉ ተደመምኩ:: «ውዶችን ያስቀይምብኝ ይሆን?» አልኩናም አሰብኩ:: ወዲያው ግን «ኤዲያ! እነሱ ከድህነትና ከችጋር አምባሳደሮች ጋር የፖለቲካ ድሪያ ሲዳሩ(ዳ ትጥበቅ) ቅንጣት ያላዘኑልኝ እኔ ለማን ጀቴ ብዬ?» አልኩ:: እናም በጀመርኩት ቀጠልኩ፤ እናንተም ውድ አንባቢዎቼ በኃይለ ቃሌ እንዳትቀየሙብኝ አደራ::

ይሄ ገንዘብ የሚሉት ነገር ምን ዓይነት ምትሃት ይሆን ያለው ? ሥልጣን የሚሉትስ ነገር ምን ዓይነት መግነጢሳዊ ኃይል ይሆን የተላበሰው? ምነው ከሁለቱ አንዱን ቢቻል ደግሞ ሁለቱንም ቢያንስ ለአንድ ጀምበር ይዤ ባየሁዋቸው! በነዚህ ዓለማዊ ተውህቦዎች የሚንበሸበሹ እንዴት ያስቀናሉ? ምን መናገር ብቻ ሳይሆን ምንና እንዴት ማሰብ እንዳለብን በመሪዎቻችን መመሪያና ሕግ በሚወጣልን ሀገር ውስጥ እዬኖርን እገሌ ወይ እነገሌ ምን ይሉኝ ሳይሉ እንዳሻቸው የመጣላቸውን ሁሉ መዘርፈጥ የሚችሉ ሰዎች በርግጥም የታደሉ ናቸው - እንዲያ እንደነሱ መሆንም መታደል ከሆነ:: እንዲህ ዓይነት ሰዎች አያስቀኑም? እነ አያ እንደልቡና እነ አጤ በጉልበቱ በርግጥም አያስቀኑም ማለት አይቻልም:: እንዲህ ዓይነት ሰዎች ስንቶቸ አሉ መሰልዋችሁ!

አንድ የወያኔ ጋዜጠኛ የነበረ ቀብራራ ዉጤት ተኮር የሆነ አስተዋይ «ጋዜጠኛ» በግዞጣ የሚያገኘው ገቢ የማያምር ሆኖ ሲያገኘው ወደ ማስታወቂያው ዞረና በዚያም ከበረና

ከብሮም ደረጃውን ለወጠና ኩራትና ስድቡ ሌልኛ ሆንዋል አሉ:: ይቺን ጦማር ካዩ «ምቀኛ!» ነው የሚለኝ መቼም - ግዴለኝም ይበለኝ:: ያገራችን መሬት ግዴላችሁም ለተሳዳቢና ለቀብራራ ብቻ ሳይሆን አይቀርም የሚመቸው:: እሱን እንተወውና ወደ ኃይሌ እንመለስ::

ኃይሌን ከልቤ እወደዋለሁ:: ልግጫ አይደለም በጣም እወደዋለሁ - ሰሞኑን ግን በፍቅሬ ላይ ነው ቀዝቃዛ ውኃ የቸለሰብኝ - ለርሱና ለጥረቱ በነበረኝ ፍቅር ላይ:: የምወደው ግን በሩጫ ያገኘው ገንዘብ ናላው ላይ ወጥቶ ኅሊናውን አስቶት በብር እንጉልፋቶ አንጎሉ ሥራውን ስላቆመና እየቀባጠረ ያለውን ባለማወቁ አይደለም፤ የምወደው - ክቡር ጠ/ሚንስትሬ የኃይሌን ለጠ/ሚንስትርነት ውድድር ማቀድ ሰምተው ተናገሩት እንደተባለው «አገር የሚመራው በአእምሮ እንጂ በእግር አይደለም» የሚለውን ሽሙጥ ያተረፈለትን ሀገር የመምራት ፍላጎቱን በማድነቅ አይደለም፤ የማከብረው ለሀገርና ለወገን የሚተርፍ የኢንቬስትመንት ሥራ በመሥራቱና ከችግር በስተቀር በሌላ እምብዝም የማትታወቀውን የሀገራችንን ሥም በተለይ በአትሌቲክስ አደባባይ በበጎ ጎን በማስጠራቱ ነው:: በሌላ በኩል ያለውና ከ«ተከድኖ ይብሰል» ደረጃ የዘለለው ሁኔታ ግን አነጋጋሪ እዬሆነ መጥቶኣል::

ኃይሌ ገ/ሥላሤ እጅግ ብዙ ጠንካራ ጎኖች ያሉትን ያህል በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እየታዩበት የመጡ ጠንጋራ ጎኖች ግን እሱን ለማያልፍ ትዝብት እኛን ደግሞ ለሥነ ልቦናዊ ጉዳት እየዳረጉን ናቸው - እኛ የምለው ሀገር እያለን በወያኔ ምክንያት ሀገር አልባ ከርታቶችና የበይ ተመልካቾች የሆንነውን ማለቴ እንደሆነ ይታወቅልኝ:: ኃይሌ ለሩጫው የሚያደርገውን አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ዝግጅት ያህል ገንዘቡ ሊያስከትልበት ለሚችለው ማኅበራዊ ቀውስና ፖለቲካዊ ጣጣ በቂ ዝግጅት ያደረገ አይመስልም:: በዚህም ምክንያት በትምህርት እምብዝም ባልገፋው ስብዕናው ላይ ይሄ የገንዘብ መቆለል አደገኛ ክስተት አጣብቂኝ ውስጥ እዬከተተው ነው:: የገንዘብንና የሥልጣንን ፈተና በአግባብ ካልተወጡት ደግሞ መጨረሻው ውርደት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው:: ገንዘብ ኅሊናን ያሳውራል፤ አቅልን ያስታል፤ እሚናገሩትን ያሳጣል፤ ከሁነኛ ሰውም ጋር ያቆራርጣል:: ገንዘብ ጤና ማግኛ የመሆኑን ያህል በሽታ መግዣም ነው:: የገንዘብ መዘዝ ተነግሮ አያልቅም:: ስንቶችን አዋርዶኣል፤ በተቃራኒውም ስንቶች ልባሞችንና አስተዋዮችን ከፍ ከፍ አድርጓል::

ሰዎች ስለኃይሌ በሀሜት ደረጃ የሚያወሩትንና ራሱም በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚናገረውን ገንዘብ ላለማውጣት የሚያደርገውን ጥንቃቄ እዚህ ላይ አልተችም - አያገባኝምም:: «ኃይሌ ቆንቋዋና ነው፤ኃይሌ ቆንጧጥ ነው፤ ኃይሌ ለድሆች ዱዲ አይደማውም፤ ቲፕ እንኳዋን አይሰጥም፤ ቢሰጥም እጅግ በጣም ትንሽ - በሣንቲም ደረጃ - ነው፤ ኃይሌ ገንዘብ ለሚያስገኝ ነገር እንጂ ለሚያስወጣ ነገር ጆሮና ደንታ የለውም፤ . . .» የሚባለው ሁሉ ትክክል አይመስለኝም:: በዚህ ረገድ ማንም በዬመንገዱ ገንዘብ እዬረጨ ስለማይሄድ የኃይሌ አቅዋም ብዙም የሚነቀፍ የለውም ባይ ነኝ:: በዚያ ላይ ኃይሌ ሩዋጭ እንጂ አበበች ጎበና አይደለም፤ ኃይሌ ለባንዲራ ፍቅር የሚሮጥ አትሌትና ብዙ ገንዘብ ለማግኘት የሚጥር ሀገር ወዳድና ሕዝብ አፍቃሪ ኢንቬስተር እንጂ የበጎ አድራጎት ሰው አለመሆኑን ልብ ይሉዋል::

« ሰው ለልማት ሲባል ቤቱ ፈረሰብኝ ሲል ያስቀኛል::»
« (ሕዝቡ) ድሪቶው ጋር ይኑር ወይም ድሪቶው ይውለቅ::»
« ክቡር ጠ/ሚንስትራችን እንዳሉት ድህነት ዋናው ጠላታችን ነው::»(የድህነትን ዋና
ጠላትነት ለማስረዳት አቶ መለስ በግድ መቆላመጥ አለበት? የምን ደጅ ጥናት ነው?)
« የኢትዮጵያ ሕዝቦች . . .»
« እኔ በማይክሮ ሰከንድ ውስጥ አንድ ሚሊዮን ዶላር አጥቻለሁ/አግኝቻለሁ::»
(የዘመናት ችግራችን በኃይሌ የማይክሮ ሰከንድ ጠቀሜታ ገለጣ ይወገድ
ይሆን? ማየት ነው)
« ይህችን ማሊያ ለጠ/ሚኒስትራችን በስጦታ እንዳበረክት ይፈቀድልኝ::»

ከዚህ በላይ የተኮለኮሉት ብርቅዬ ዐረፍተ ነገሮች ከብርቅዬው አትሌታችን ከኃይሌ ገ/ሥላሤ አንደበት የወጡ ናቸው:: በወጣትነቱ ራሱ ሮጦ በስተርጅና ሕዝብን ለማሯሯጥ የጠ/ሚኒስትርነትን ህልም ያነገበ የሥልጣን ተስፈኛ እነዚህን ቀርቶ ሌላም ቢል ያምርበታል:: መጥኔ ለኛ እንጂ - የመጣውን ሁሉ ለምንሸከም::

ለኃይሌ የምለው አለኝ:: «ቀጥኜ ቢያዩኝ ጅማት ለመኑኝ::» ይባላል:: እንዴት ብትንቀን ነው እንዲህ የምትሳለቅብን? የነ መለስ ቀልድና ስድብ አይበቃቸውም ብለህ ይሆን? ደግሞስ ደሪቶኣም ሕዝብ ለመምራት ማቀድህ ለምን ይሆን? ለመሆኑ ስንተኛ ክፍል ድረስ ተምረሃል? ምነው ወጥ ረገጥህ ኃይሌ? ምን በደልንህ? «አይዞህ ፤በርታ፤ግፋበት» እያልን ድልህን በሞራል ማጀባችንና ማበረታታችንን ነውር ሆኖ ይሆን በጭቃ ጅራፍህ የምትሸነቁጠን? እስኪ መጀመሪያ ቤትህን ባግባቡ ምራና - እንደሩጫው ሁሉ በትምህርቱም ጥቂት ግፋና - በዕድሜም ጠና በልና ከጠላቶቻችን ጉያም ውጣና ያኔ ለማንኛውም ነገር ያደርስሃል:: አሁን የምን መንቀዥቀዥ ነው? እኛንም አመድ አፋሽ የሾተላይ ምርኮኛ አታድርገን:: ጥጋብህና ገንዘብህ ያመጣብህን ዕብሪት የሚያስችል አቅምና ልቦና እንዲሰጥህ ፈጣሪህን ለምነው::

በጣም የሚቆጨው ከአንተ የተሻለ ሰው የታጣ ይመስል ለጠ/ሚኒንስትርነት እወዳደራለሁ በማለት የአእምሮ ብስለትህን ሳይሆን የሩጫ ጥበብህን ተመርኩዘን እንደምንመርጠህ ገምተህ (ም ይጥበቅ) ሥልጣን ለመያዝ ማቁብቁብህ አይደለም፤ አሁን እያወረድክብን ያለው የስድብና የንቀት ቱማታ ነው ክፉኛ እያንገበገበን ያለው:: እኛ ያጣነው እውነተኛ ዴሞክራሲ እንጂ የሚያፌዙብንን መች ሆነና ቀድሞ ነገር:: ሀቀኛው የምርጫ ወቅት ሲመጣ አንተም እንደማንኛውም ዜጋ እኩል መብት ያለህ ነህና ያኔ ትወዳደራለህ:: አሁን ግን ግዴለህም ዝም ብለህ ሩጥ፤ ኢንቬስትመንትህንም አሯሩጥ:: እኛን ካልተሳደብክ አሳዳሪዎችህ አናሠራህም ብለውህ ከሆነ ችግር አለ ማለት ነውና እሱን ለሚመለከተው አቤት በል:: እኛን ግን ለቀቅ አድርገን:: በኛ ሂሳብ ቆዳህን ልታዋድድ ፈልገህም ከሆነ በተለይ ባንተ አያምርም - ስንተዋወቅ? እስኪ አስታውስ - በፊት በፊት ከድል በሁዋላ የትኛ ዋን ባንዴራ ነበር የምታውለበልብ? አሁንስ? ደባደቦ ያለበትን የወያኔ የፈጠራ ባንዴራ አይደለም ፈልገህ የምታውለበልብና የምትለብስ? ብቻ ይቅር የያዘ ይዞሃል አሁን:: የሆነ ሆኖ ድህነትን ከኛው ባልተናነስ በልጅነትህ ሳትቀምሰው አልቀረህምና በሱ ይሁንብህ የዛሬን ማረን:: ምን አልንህ? ማፍቀርና መውደድ ሊያሰድብ ይገባል? ግፍስ አይሆንብህም? ለ«ልጆችህ»ስ ግፍ ማኖሩ አንተን አያስወቅስህም? እንደምትወደን በዕንባ ጭምር አልነበር የምትገልጽን? የአዞ ዕንባ ነበር ማለት ነው? ምን ነካህ? ምንስ አዞሩብህ? በጥሞና አስብበትና ሳይረፍድ ወደ ኅሊናህ ተመለስ:: ይህን ዕወቅ - ሀብት አይጠገብም፤ ሥልጣን ያጓጓል፤ የሁለቱም የጋራ ባሕርይ ግን ገደብ ካላበጁላቸው ገደል ይከታሉ:: አንተም ከዚህ ብዙዎች ወንድምና እህቶቻችንን ከገበርንበት መጥፎ አዙሪት እንድትወጣ ነው ይህችን አጭር ጦማር መጦመሬ::